Date: 02/12/2015

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር(ኢ.ሕ.አ.ግ) የተሰጠ መግለጫ
ለአሉባልታ የምናጠፋው ጊዜ የለም!!

በዚህ በተያያዝነው ዕልክ አስጨራሽ የትግል ወቅት፣ የተሠማሩበትን የትግል ሂደት ቁልጭ አድርገው የሚያውቁ ግለሰቦች፣ ጥበብን ከትምህርትና ከልምድ ያካበቱ፣ የወያኔን መሠሪነትና አገር አውዳሚነትን በቅጡ ይተረዱ፣ የዓላማ ፅናት እንዲሁም ጥራት ያላቸው፣ መዳረሻችንን በውል የሚያውቁና ሃላፊነት የሚሰማቸው ቢያስተምሩና ቢመሩ ኢ.ሕ.አ.ግ ደስተኛ ይሆናል። ደስተኛ የማይሆነው፣ የአመራር መድረኩ ብቃት ለሌላቸው አስመሳዮችና ሠርጎ-ገቦች እየተለቀቀ፣ ደግመው ደጋግመው አገራችንን መቀመቅ ለመክተት እንደልባቸው ሲፈነጩና የ85 ሚሊዮን ሕዝባችንን ኅልውና እንደገና አደጋ ላይ ለመጣል ሲሸርቡ ብቻ ነው። ሰሞኑን ዘረኛውና ግፈኛው ወያኔ የተለጣፊ መንጋን አሰባስቦ፣ አጨብጫቢዎችን ለመለስና ለአዜብ የቤተሰብ ጥምር መንግሥት አገልጋዮች እንዲሆኑ መርጧል። ከፓርቲ አመራርነት ለቀቁ ወይም በጡሮታ ተወገዱ የተባሉትም ጠቀም ያለ ቤትና ገንዘብ ተለግሷቸዋል። እኒህ ግለሰቦች ቀድሞውንም ቢሆን ሥልጣንን መከታ በማድረግ የናጠጡ ሃብታሞች እንደሆኑ የታወቀ ነው። ይህ የአሁኑ የሹም-ሽር ክስተት ለማደናገር ካልሆነ በስተቀር፣ አዲሶቹና ቀደምት ወያኔዎች አደገኛ የሆነውን ሚስጢራዊ-ወያኔያዊ ተግባራቸውን ከመጋረጃው በስተጀርባ ማሤራቸው የማይቀር ነው፤ ስለዚህ ክስተቱን አልሸሹም ዞር አሉ ነው ብንል ስህተት አይሆንም።

የደሮ ዐይን የዋጠው ወያኔ፣ ነገም ቢሆን በተለመደ ማደናገሩ ይገፋበታል—በሕዝብ ክንድ ተመትቶ እስተሚወድቅ ድረስ! ዘረኛው የገዢ ቡድን እስከዛሬ ድረስ የፖሊሲ ለውጥ አድርጎ አያወቅም፤ ወደፊትም አያደርግም። ለምን? ቢሉ፣ መልሱ—የመማር ችሎታ በፈጣሪያችን አልታደለውማ! የተጠናወተው የዘር ልክፍት አሳዳጭሮ እራሱንና አጋሮቹን ሳያጠፋ፣ በአገራችን መሠረታዊ ለውጥ ይመጣል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። ከበረሃ ጀምሮ አገር በማውደም ተግባራት ላይ ተሠማርተው የነበሩት ባልደረቦቹ ይቅርና፣ እራሳቸው መለስና አዜብ በጡረታ ቢገለሉም እንኳን፣ መንግሥትና የአገሪቱ ሕዝብ በዘር ተደራጅቶ እስከቀጠለ ድረስ፣ የምንናፍቀው ለውጥ ሊመጣ ይቅርና የለውጥ ሽታውም እንኳን በትንሹ ሊሸት አይችልም። የተደረገው የግለሰቦች የይምሰል ሹም ሽር፣ ጥገናዊ ለውጥ እንዲያደርጉ ሲገፋፏቸው የነበሩትን የውጭ አገር ጌቶቻቸውን ጫና በመጠኑም ቢሆን ይቀንስላቸው እንደሆን እንጂ፣ ሕዝባችን ከሚመኘው ጉዙፍ ለውጥ ቅንጣት የምታክለውን እንኳን ሊያመጣ አይችልም። ስለዚህ አጃን ወግጠው ቢዘሩ ገባ ከዘሩ መባሉ አይቀሬ ነው።

በኢትዮጵያውያን ጫንቃ ላይ የሚጫኑት አዲሶቹ ምልምሎች፣ ይበልጥ ለመለስ ፀጥ-ለጥ ብለው የሚገዙ ዘመናዊ አጎብዳጆች ናቸው። እነዚህ ምልምል የቤተመንግሥት ባሪያዎች በወያኔው መሪ ስብከት ደንቁረዋል! ይበልጥ በደነቆሩ ቁጥር፣ ይበልጥ ይገዙለታል! ሕዝባችንንም መልሰው በማደንቆር ዝንተዓለም ነፃነትን ሳያይ ተገዢ እንዲሆን ያደርጉታል። ከሥልጣን ወረዱም ተባሉ በጡረታ ተገለሉ፣ ወያኔ ወያኔነቱን አይቀይርም። ሃብት አካበቱ አላከበቱ ሕመማቸው ዘረኝነት ስለሆነ፣ ከምድር ገፅ ካልጠፉበስተቀር በሽታቸው ፈውስ የለውም። ወደ ምሥራቅ ሄዱ ወደ መዕራብ፣ ዘረኞች ዘረኝነታቸውን አይተውም—እስከ አጥንት ደም-ሥራቸው ድረስ ዘረኝነት፣ ኢሰባዊነትና ነጣጣይነት ተጣብቷቸዋልና። ስለዚህ፣ ምክር ቤቱ ሙሉ በሙሉ በወያኔ ስለተያዘ፣ አምባገነናዊ የዘር ሥራርዓቱ ይበልጥ ተጠናክሮ፣ ሥልጣንና የአገሪቱ ጥሪት በአንድ ቤተሰብ ቁጥጥር ሥር ከመዋሉ በስተቀር በአገራችን የተለወጠ አንዳችም ነገር የለም።

ፈረንጆቹና ቻይኖቹማ፣ ግፈኛውን ለዚህ ያበቁት እነርሱ ስለሆኑ፣ አለችኝ የሚላትን ፀጉሩን ቢከረክሙት፣ ቅንድቡን ቢኩሉት፣ የሌለውን ቁመት ሊቀጥሉለት ቢሞክሩም፣ ፊቱን ቀባብተው ሊያስቆነጁት ቢጥሩም፣ እራሳቸው የፈጠሩትን ትንሽ ጋኔል ለማስዋብ የሚያደርጉት ስለሆነ ከቶ አይገርመንም። ከፈለጉ የታሪክ መስታወት ሰጥተን፣ አስቀያሚ ገፅታውን በገዛ እራሱ እንዲያየው ማድረግ ግን እንችላለን፤ ዐይቶ የሚያመዛዝን አዕምሮ የለውም እንጂ! ለአብነት ያህል፣ ሰሞኑን የኮሎምቢያ ዩኑቨርሲቲ፣ ኃያሉ ፈጣሪያችን ለዘረኛው ያልሰጠውን ስጦታ እንደተሰጠው አድርገው ግራማ ሞገስ በማጎናፀፍ፣ ጥበበኛ ለማስመሰል አግዝፈው፣ ከአፍሪካ ሕዝብ በላይ ቁብ አድርገው የሣሉትን ሥዕል ያሰተወሷል። እኒህ ሰዎች ዕውን እንደሰው ያስባሉ? በዕብሪት የደመሰሰውን ሕዝብ፣ ያሠረውን ወጣትና አዛውንት፣ በጦርነት ያስጨረሰውን ወገን፣ የዘረፈውን ንብረት፣ ያፈነውን መብት፣ ያስራበውን ወገን፣ ያነጣጠለውንና ያፋጀውን ሕዝብ፣ ያስደፈረውን ዳር ድንበርና የተዋዋለውን የአገር ክህደት ውል የማያውቁ ሆነው ነው ወያስ የሠራውን ወንጀል ተገቢና ሕጋዊ መሆኑን ሊያረጋግጡለት ፈልገው? ለጊዜው በሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን በደል ሙሉ በሙሉ ማስቆም ባንችልም፣ የተፈቀደና መሆን ያለበት ሕጋዊ እርምጃ ተደርጎ እንዳይቆጠር ግን ቢያንስ አጥብቀን እንቃወማለን! ለመሰረታዊ ለውጥም እንታገላለን!

ይህን መግለጫ እያነበብን ባለንበት ስዓት፣ ኢ.ሕ.አ.ግ በሰሜን ጎንደር በወያኔ ላይ ከፍተኛ የማጥቃት  ውጊያ እያደረገ ይገኛል። በ1983 ዓ.ም፣ ወያኔ ቤተመንግሥቱን ከተቆጣጠረበት ዕለት ጀምሮ፣ ኢ.ሕ.አ.ግ ከወያኔ ጋር የአፈሙዝ ፍልሚያ ማድረጉን እስካሁን እንደቀጠለበት ነው። ይህን ሃቅ አንዳንድ ወስላቶች ቢክዱትም ወይም ቢያውገረግሩትም ቅሉ፣ በሃገር ውስጥና ውጭ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም በአጎራባች አገሮች ያለው ሕዝባችን አሳምሮ ያውቀዋል። ወያኔና ኢ.ሕ.አ.ግ ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቀው የተዋጉት በርካታ ጊዜ ነው፤ ወያኔም እስከአህን ድረስ ከፍተኛ ኪሣራ እየደረሰበት ይገኛል። ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም የሚታገሉ ድርጅቶችን፣ ኢ.ሕ.አ.ግ ጠንክራችሁ ታገሉ፣ ከጎናችሁም ነን ብሏል። እኛ የትግል አጋራችሁና ደጋፊያችሁ ነን እንጂ ጠላቶቻችሁ አይደለንም በማለት መግለጫ አውጥቷል። የሰላም ትግሉ ቢሳካ እንኳን በማለት፣ በ24 ስዓታት ውስጥ፣ በገዛ ፈቃዳችን ብረታችንን አውርደን፣ የሰላም ዘንባባ ይዘን እንደምንቀርባቸው አውጀናል።

በ2002ቱ ምርጫም፣ መራጮችንና ተመራጮቹን ማስፈራራቱ፣ መብት ግደባውና ግድያው በድጋሚ ተከስቷል። ወገናችን በሚችለው የሥራ  መስክ ሠርቶ ማደር ሰባዊ መብቱ መሆኑ እየታወቀ፣ ሥራ ለማግኘት የግድ የወያኔ አባል ሆኖ ወያኔን ካልመረጠ፣ እየሠራ የመኖር ዕድሉ የመነመነ እንደሚሆን ተነግሮታል፤ ይህ ቀጥተኛ ማስፈራራትና የግለሰብ ነፃነትን መግፈፍ ነው። ወያኔ ወገናችንን በማስፈራራት

ሥራን ለፖለቲካ ፍጆታ ተጠቅሞበታል፤ ስለዚህ ምክርቤቱም ሆነ ሹም-ሽሩ አስቂኝ ድራማ ነው ብንልም ቅሉ፣ ሕዝባችን ግን የወያኔን መሠሪ ተግባር በሚገባ ዐውቋል፤ በተደጋጋሚ የሚታለሉለት ግን ሆዳሞችና የዋሆች ብቻ ናቸው። አሁን ግን፣ ከ2002 ዓ.ም ምርጫ በኋላ በርካታ ኢትዮጵያውያን ኢ.ሕ.አ.ግን በመቀላቀል ሠራዊቱን እየገነቡት መሆኑን በውጭ ሃገር ያለው ሕዝባችን ሊያውቀው ይገባል እንላለን። እኒህ ወገኖቻችን የሰላም ትግል ማድረግ ይቻላል ብለው በማመን አገርቤት ውስጥ የተደራጁ ነበሩ። ሁኔታው ተለውጦ ወያኔ ወደ ፍፁም የባልና ሚስት አምባገነንት ሲለወጥ፣ ያውም ሥልጣን በአንድ ግለሰብ እጅና ፈላጭ ቆራጭነት መግባቷን ስላወቁና የዴሞክራሲ በር ክርችም ብሎ ስለተዘጋ፣ አሁን የኢ.ሕ.አ.ግን ሠርዊት በሠፊው በመቀላቀል ላይ ናቸው። ከተለያዩ በሰላም ወይም ሕጋዊ ትግል ከሚታገሉ ድርጅቶች የተውጣጡ፣ ዛሬ በቀን እሰከ 30 ሰዎች ኢ.ሕ.አ.ግን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ።

ኢ.ሕ.አ.ግ በፖለቲካው መስክ ማስተማርን፣ በተቋም እረገድ ሠራዊቱን በመገንባት፣ ሠፊውን ሕዝብ በሕቡዕ በማደራጀት እንዲሁም የትጥቅ ትግሉን በመምራት ሁለገብ የትግል እርብርቦሽ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህም አደረጃጀት ዳር እስከ ዳር ያሉትን ኢትዮጵያውያን ያካትታል። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ቁም ነገር አለ—አገራችን በርካታ የድርጅት ዛፎች አሏት፤ ዋናው ጥያቄ የዛፉ መኖር አለመኖር አይደለም፤ መጠየቅ ያለበት ጉዳይ፣ "ዛፉ መልካሙን ፍሬ እያፈራ ነው ወይ?" ነው። ምክንያቱም ዛፉ ሳያፈራ ለእራሱ ብቻ መኖር ይችላልና። ዛፍን ካነሳን አይቀር፣ የወያኔ ዓይነት መርዘኛ ዛፍም አለ። የኢ.ሕ.አ.ግ የድርጅት ዛፍ ግን አዝርዕቱን በህዝባችን ውስጥ በመዝራት፣ ጊዜው ሲደርስ እያንዳንዱ አዝርዕት በማደግ ያብባል፣ መልካሙን ፍሬም ያፈራል—በጀግኖቻችን አጥንትና ደም ተኮትኩቶ! ይህ ሃቅ ነው! በዚህ ተግባርም የወያኔን መርዘኛ ዛፍ ሥር አልባ እንዲሆን ይደረጋል፤ ሥር የሌለው ነገር መፍለሱ አይቅሬ ነውና! ለዚህ ጉዳይ ለምስክርነት የሚቀርቡት ዘረኞች ሳይሆኑ የሰማዕታቱ አጥንትና ደም ነው። ኢ.ሕ.አግም በአሁኗ ደቂቃ በከፍተኛ የጦርነት ግብ ግብ ላይ ነው ያለው። ውጊያ መደረጉን ካልሰማሁ፣ ጦርነቱ አልተደረገም ብሎ መደምደም ትልቅ ስህተት ይሆናል። ብስል የሆኑ ሰዎች እንዲህ አርገው ማሰብ የለባቸውም እንላለን። እኔ ከጠገብሁ፣ ሁሉም ሆዱ ሞልቷል ወደሚለው መደምደሚያ ዓይነት እንዳይደርሱ በመስጋት!

እንደዕውነቱ ከሆነ ኢ.ሕ.አ.ግ የግለሰቦችን ስም እየጠራ ስም የማጥፋት ዘመቻን አይወድም። አልፎ አልፎ ሁኔታው አስገድዶን መልስ ለመስጠት ሲባል ብቻ ካልገባንበት በስተቀር፣ በመሠረቱ ፍላጎታችን ግን አይደለም። የወያኔ ቅጥረኞች ግን ለሚቃወማቸው ሁሉ ያደርጉታል፤ ዋናው አላማቸው አሉባልታ በመንዛት ሕዝብን ለማወናበድና ለማሸበር ነው። ይህን ተግባር የሚያራምዱት ዕድሜ ቀጥል ካድሬዎቻቸው ናቸው። በጥቁር ጫካ የቀረበውን ፅሑፍ ያነበባችሁ ግን ትዝብት እንድትወስዱ ከማሳሰብ ይልቅ ሌላ ምንም ማለት አንችልም። በድሕረ-ገፁ ላይ የወጣው ፅሑፍ፣ የውጭና የውስጥ ጠላቶች በሙተባር በኢ.ሕ.አ.ግ ላይ እንደተረባረቡበት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ ቢያንስ ቢያንስ ለእኛ ግልፅ ነው። ወያኔ ቆርጦ የሚታገለውን ድርጅት ሆነ ግለሰብ፣ ቢችል በጦር ወግቶ፣ በስውር ገድሎ ወይም ዕድሜ ልክ አሥሮ ደብዛውን ከማጥፋት ወደኋላ የማይል ጉደኛ ፍጥረት መሆኑ የታወቀ ነው። በቅጥረኞቹ አማካኝነትም የስም ማጥፋት ዘመቻ ያለማቋረጥ ያካሂዳል። በዚህ አኳያም የጥቁር ጫካ ትረካ ወያኔያዊ ተልዕኮ ያለው መሆኑን ለማወቅ ጠለቅ ብሎ ማንበብን ይጠይቃል። ኢ.ሕ.አ.ግ በበኩሉ ለአሉባልተኞችና ለወሬ ለቃሚዎች የሚያጠፋው ትርፍ ጊዜ የለውም። ከወሬኞች፣ ከፈሪዎች፣ ከቅጥረኞችና ከወላዋዮች ጋር በእሰጥ-አገባ መነታረኩ ፋይዳ የለውም። ስልቻ ማልፋት እንዲሉ፣ አንዴ ቢሞክሩትም አሉባልታው ብሶ ተባብሶ መምጣቱ አይቀሬ ነውና። ስለዚህ በዋና ዋና ተግባራት ላይ በማተኮር፣ ዓላማን ለማሳካት ጠንክሮ መሥራቱና ውጤትን ማስመዝገቡ የተሻለ ነው ብሎ ኢ.ሕ.አ.ግ ያምናል። ስለፅሑፉ በዝርዝር ብዙ ማለት እንችላለን፤ ነገር ግን ለጊዜው ትንሽ ብለን ብንገታው የሚሻል ይመስለናል።

ካለፈው ወር ጀምሮ፣ ጥቁር ጫካ በሚል የብዕር ስም፣ በተከታታይ በኢትዮሜዲያ ድሕረ-ገፅ ላይ ስለኢ.ሕ.አ.ግ የወጣው ፅሑፍ አንዳንድ ዕውነታዎችን የተመረኮዘ መስሎ ቢታይም፣ በርካታ ሃሰቶችንና የስም ማጥፋቶችንም ዘግቧል። ለምሳሌ፣ የተጠቀሱት ሁለት ግለሰቦች የሠራዊቱ አመራር ነበሩ ያለው ትልቅ ውሸት ነው፤ እኒህ ግለሰቦች የሠራዊቱ ከፍተኛ አመራር ሆነው አያውቁም። በፅሑፉ ከተጠቀሱት ሁለት ግለቦሰች ሌላ፣ ወደ ውጭ አገር ድርጅቱን ለማስተዋወቅ የመጣና ወደ ሜዳ የተመለሰ ሰው የለም ያለውም ሌላው ትልቅ ውሸት ነው። ሜ. ጄኔራል መስከረም አታላይ፣ ሁለት እራሱን ሆኖ በመምራት ወደ አሜሪካ አገር ከመጣ በኋላ፤ ተግባሩን ፈፅሞ ወደ በረሃ በመመለስ፣ ወታደራዊ ግዳጁንም አከናውኗል፤ የአካል መቁሰል አደጋ ከደረሰበትም በኋላ ለሕክምና ወጥቶ፣ አሁን ግን ከውጭ ሆኖ የማደራጀት ሥራውን በመሥራትና ሠራዊቱን በመምራት ላይ ይገኛል። አብዛኛውን በውጭ ሃገራት፣ በተለይም በአውሮፓና አሜርካ ያሉትን ደጋፊዎች ያሰባሰባቸው እራሱ፣ ሜ. ጄኔራል መስከረም አታላይ ነው። በውጭ አገር ያለውን ኮሚቴም አሰባስቦ ባንድነት ሲመራ ቆይቷል፣ አንዳንዶቹ የትግሉ ማዕበል ሲገርፋቸው ቢደናገሩም ቅሉ።

የመምራት ችሎታ አላቸው ተብለው በፅሑፉ የተጠቀሱት ግለሰቦች፣ ያን ዓይነት ችሎታ በፍፁም የላቸውም። ወቅቱ ለሚጠይቀው፣ ኃይልን በማንቀሳቀስ የሽምቅ ውጊያን መምራት ለየት ያለ ችሎታ፣ ቆራጥነትን፣ አመች ቦታ መምረጥን፣ የሽምቅ ውጊያ ልምድና ከአካባቢው ሕዝብ ድጋፍ ማሰባሰብ በሚችሉ መሪዎች መመራት እንዳለበት የታወቀ ነው። ያኔ በጀማሪነት ደረጃ ያለን የሽምቅ ተዋጊ ኃይል ለመምራት፣ ከግለሰቦች ችሎታና ከሚያስገኙት ጠቀሜታ ይልቅ፣ ፀሐፊው በጎጠኝነት ስልጣን እንዲይዙላቸው የሚፈልጓቸው ሰዎች ያሉ አስመስሎባቸዋል፤ ምኞታቸው ይህ ከሆነ በጣም ያሳዝናል እንላለን። ችሎታ አላቸው የተባሉት አውሮፕላን አብራሪም፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን የሽምቅ ውጊያ ስልት፣ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የሕዝቡን አሰፋፈርና ስነልቦና በቅጡ አያውቁትም። በተጨማሪም ኡጋንዳ ተመድበው ምን ይሠሩ እንደነበር የሚያውቁ ያውቁታል። ታሥረዋል፣ የቁም እሥረኞች ናቸው የተባሉትም ሃሰት ነው። ከዚህ ቀደም እስከ 30 የሚሆኑ ሰዎች፣ የተጠቀሱትን ግለሰቦች ከሚኖሩበት አገር ሄደው የኑሮአቸውን ሁኔታ ታዝበው መጥተዋል። ሌሎቹም በግል ጉዳያቸው በተለያይ ጊዜ የሚሄዱ ሰዎች አኗኗራቸውን ያውቃሉ።

የወያኔ ተልዕኮ ካለው ስም-አይጠሬ ከሚተርክልን ትረካ ይልቅ፣የሚያውቁ የዐይን ምስክሮች በገሃድ ወጥተው ሃቁን ቢነግሩን ይሻላል። የሚሉሽን ብትሰሚ ገበያ ባልወጣሽ እንዲሉ፣ ስለሰዎቹ ጨርሰን እንድንናገር አትገፋፉን እንላለን። አየር አብራሪው፣ ባሉበት አገር ፉርኖ ቤት ከፍተው፣ ምን የመሰለ መኪና ገዝተው እየዘነጡ የሚኖሩ ናቸው። የኢ.ሕ.አ.ግ ሠራዊትማ የድርጅቱን ንብረት ለግል

ጥቅማቸው ሳላዋሉት፣ ጊዜው ሲፈቅድ ለፍርድ እናቀርባቸዋለን ይላል። ሕዝቡም ለትግሉ ያዋጣው ገንዘብ ለግል ጥቅም በመዋሉ ተጠቃሾቹን ፍርድ ፊት መገተሩ የማይቀር መስሎ ይሰማናል። ካልተረሳ፣ የነፃነት አርበኝነት አሳርና ፍዳን አስበልቶ የሚገኝ ነው ብለናል። የድሮው ሲገርመን፣ አርበኝነት አየር በአየር እንዲሆን ፈለጉ እንጂ ፀሐፊው? ድሙት መንኩሳ አመሏን አትረሳ ይሏችኋል ይህ ነው። ኢ.ሕ.አ.ግ ትግሉን በማጧጧፍ፣ ሕዝባችንን ከጎኑ በማሰልፍ፣ የማታ ማታ አሉባልተኞችን፣ የጠላት አጋሮችንና ትግል አምካኞችን ጀግናው ሕዝባችን በድል አድራጊነቱ ያሳፍራቸዋል። ቸሩ ፈጣሪያችንም የሕዝባችንን የሲቃ ድምፅና ልመና ሰምቶ መርዳቱ ግን አይቀርም። ያም ሆነ ይህ፣ ለጊዜው ዕውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል በሚለው እንድንስማማ እንጠይቃለን።

ሜ. ጄኔራል መስከረም አታላይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ሊቀመንበር፣ በውጭ አገር ያሉ የኢ..ሕ.አ.ግ ኮሚቴዎች የሚያደርጉትን ሽኩቻ፣ አለመግባባትና ስም ማጥፋቶች ከመሠረቱ ማስወገድ የሚቻለው በጠቅላላ ጉባኤ ነው ብሏል፤ ለሚገባው ሰው ይህ ትክክለኛ አሠራር ነው። የችግሮችን መንሴ ለይቶ በማወቅ፣ መፍትሔውም እንዲፈለግ ጠቅላላ ጉባኤ መጠራት አለበት፤ ለዚህም ጄኔራሉ አጥብቆ እየሠራ ይገኛል። የድርጅቱን አመራር ሰንሰለትና የሥራ ክፍፍል አስተካክሎ በማዋቀር፣ የድርጅቱንም ነፃነት ለማስጠበቅ አስቸኳይ ድርጅታዊ እርምጃወች መወሰድ እንዳለበት በተገኘው የብዙኅን መገናኛ ግልፅ አድርጓል፤ ዋናው ጉዳይም ይህ ነው። አርበኛው ለመውጫና መግቢያ የሚያገለግለውን አገር መምረጥ ድርጅታዊ መብቱ መሆኑም ተገልጿል። ለአብነት ያህል ሱዳንን ስንጠቀም ነበር፤ አሁንም የሚያስተናግደን የጎረቤት አገር አገኘን ማለት የአገርን ጥቅም አሳልፈን እንሸጣለን፣ የአገራችንን ልዕልና እናስደፍራለን ማለት ግን ከቶ አይደለም። ይህ ከመሆኑ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለጉዳዩ ይመክራል፤ መምከር መብቱ እንደሆነም አሳምረን እናውቃለን፤ ማንስ ሊከለክለው? የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትም ኢ.ሕ.አ.ግ ያከብራል። ከጥረታችን በኋላ ሁኔታው ካላማረ፣ ኢ..ሕ.አግ በሚቀጥለው እረድፍ ያለውን አማራጭ ለመውሰድ ይገደዳል። የአገራችንን አንድነትና ብልፅግና ዕውን ለማድረግ፣ ፍትሐዊ ሥርዓትን ለማስፈንና የዜጎችን ዕኩልነት ለማረጋገጥ በመጀመሪያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ይኖርበታል። ይህ ሥርዓት በገዛ እራሱ ተሠርቶ አይጠብቀንም። እግረ-መንገዳችንን—እየወደቅን ግን እንደገና እየተነሳን፣ እየሞትን ግን በኗሪዎች ላይ ሕይወትን እይዘራን፣ እየተሰደድን ግን ለመብታችን እየጮህን፣ እያመፅን ግን ዘረኞችን እያስደነገጥንና እያንበረከክን፣ እየተራብን ግን ሕዝባችንን ለማጥገብ ጠንክረን ስንሠራ ብቻ ነው ሥራዓቱ የሚገነባው። ሥርዓት በዕውቀት ይሠራል! በጀግኖች ደምና አጥንት ተለስኖ!

መቸም ውሸት ከሃቅ ይልቅ በተሎ ትሠራጫለች፤ በማሸርገድ የሚቀበሏትም በርካታ ናቸው። ውሸት ተደላድላ የምትኖረው ለሃቅ ቦታዋን እስከምትለቅ ድረስ ነው። ዕድሜ ልክ ሙሉ የሰማነው በአብዛኛው ውሸትን ነው! ያሳዝናል!! የአምባገነኖችንና የዘረኞችን ወሸት ለማሰራጨት የሚሽቀዳደሙ በርካታ ናቸው። ግፈኛው ነፃነትን ገፎ፣ አገርን ከፋፍሎና ሕዝብን አናክሶ ስልጣኑን ለማራዘም አሁንም የውሸት ምርት በማምረት ላይ ነው። ይህን ይስልጣንና የነዋይ ጥሙን ለማርካት፣ የንግሥናውን ዘመን ማራዘም ይፈልጋል፤ ውሸትንም እንደ ዓይነተኛ የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ መሣሪያ አድርጎ ይጠቀምበታል፤ ሌሎቹም ቀደም ብለው ስላደረጉት! ዘረኛው አስከፊ ጭፍጨፋዎችን ፈፅሟል፤ በአጭሩ ግልገሎችን ከእነነብሳቸው የሚውጥ የዱር አውሬ ሆኗል ብንል ስህተት አይሆንም። እስቲ ተመልከቱ እሰከዛሬ ድረስ ስንቱን እንደዋጠ? የጫካው አውሬ የአገራችን አልፋና ዖሜጋ እራሱ ብቻ እንዲሆን ይመኛል—ሁሉም እንዲንበረከክለት! ሁሉም ያለእርሱ ፈቃድ እንዳይሠራ! ሃብትም፣ ፍትሕም፣ ጉልበትም የዱር አውሬው ብቻ እንድትሆን! የምናስበው በእርሱ ጭንቅላት ብቻ እንዲሆን! እርሱ የለም ማለት ኢትዮጵያ የለችም ማለት ነው ሊለንም ይቃጣዋል። ይህ ዕብደት ነው! ዕብደቱ ግን ዕውን እንዲሆን የሚቃዡ አሽቃባጮችም አሉት፤ አሳምረን እናውቃቸዋለን። የኢ..ሕ.አ.ግ ታሪክ ሠፊ ነው፤ የጀግኖቻችን ገድል ለትውልድ እንዲተላለፍ ታሪክ ተመራማሪዎች ትኩረት ሰጥተው እንዲፅፉት እናበረታታለን። እኛ የምንለውን በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክ አጣማሚዎች የሚሉትን በማነፃፀር፣ የአጣማሚዎችን ጉድ ዘርዝረው ለሕዝብ እንዲያጋልጡ ሃቀኛ ታሪክ ፀሐፊዎችን እንጋብዛለን።

የኢ..ሕ.አ.ግ አመሠራረት አጭር ታሪክ እንደሚያትተው፣ ከፋኝ ተብሎ  የሚጠራው የሕዝብ አመፅ፣ በገዛ ሃገሩ ወስጥ መሸጎ፣ ከወያኔ ጋር መፋለም የጀመረው ገና ደርግ በሥልጣን ላይ እንዳለ ነበር ይላል። በ1983 ዓ.ም( እ, ኢ. አ) በሰሜን ጎንደር ወያኔን ይዋጋ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (በግምት አንድ ሺ የሚሆኑ) ከፋኝ ተብሎ የሚጠራውን የሕዝብ አመፅ ተቀላቀሉ። ይህ ጦር በፀለምት፣ በወልቃይት፣ በጠገዴና በአርማጭሆ ውጊያ ከፍቶ ከፍተኛ ጥቃት በወያኔ ላይ አድርሷል። በ1984 ዓ.ም ከፋኝ ሰልጥኖና ተጠናክሮ፣ መርሃ ግብር ነድፎ፣ አመራር ሰይሞ--- ከፋኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ንቅናቄበሚል ስያሜ ተቋቋመ።ይህን የሕዝብ ንቅናቄ በማደራጀትና በማዋጋት እንዲሁም በሊቀመንበርነት የመራው የአሁኑ ሜ. ጄኔራል.መስከረም አታላይ( በዚያን ጊዜ ግን ኮማንደር ) ነው። በ1985 ዓ.ም ወያኔ የአ.አ ዩኑቨርሲቲ ተማሪዎችን በመጨፍጨፉ ምክንያት፣ ከዚያም በኋላ በርካታ አየር ወለዶችና ከተለያዩ ወታደራዊ ክፍሎች የመጡ፣ ከሕዝቡና ከእራሱ ከወያኔ አካላት ሳይቀር ከፋኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ንቅናቄን ተቀላቅለው ሠፊ አስተዋፆ አድርገዋል፤ እስካሁንም ድረስ አመራር በመስጠት ላይ የሚገኙም አሉ።

በ1987 ዓ.ም ሱዳን ወስጥ ከፍተኛ ጉባኤ ተደርጎ ታላቅ ሥራ ተከናውኗል፣ በዚህ ጉባኤ የተከበሩ ሌ. ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴ ተመርጠው፣ የድርጅቱ ለቀመንበር በመሆን ለሁት ዓመታት አገልግለዋል። በዚህ ወቅት ድርጅታችንን መልሶ በማጠናከር አገር ቤት ውስጥ የግንኙነት መሥመሮቻችንን ለመዘርጋት በቅተናል። በ1988ዓ.ም በተለያዩ የሱዳን ከተሞች ፅ/ቤቶች ተከፈቱ፤ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊት በፀለምት፣ በወልቃይት፣ በጠገዴና በአርማጭሆ በማሠማራት፣ በአገራችን መሬት ላይ ትላልቅ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ተደረጉ።  በ1989ዓ.ም ሠራዊቱ በጉባኤ በማድረግ ሜ. ጄኔራል መስከረም አታላይን መርጦ፣ የተከበሩ ሌ. ኮሎኔል ዕምሩ ወንዴን በመተካት ትግሉን እሳካሁን በማስቀጠልና በመምራት ላይ ይገኛል። አንድ ሌላ በኢትዮጵያ ውስጥ እራሱን ችሎ ይንቀሳቀስ የነበረ ድርጅት—የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር የሚባል ነበር። መጋቢት 22 ቀን 1991 ዓ.ም፣ አንድ ሳምንት ሙሉ የፈጀ ውይይት በማድረግ፣ እነህ ሁለት ድርጅቶች—(የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባርና ከፋኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ንቅናቄ) የዓላማ ተመሳሳይነት ስላላቸው፣ በስምምነት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች አንድነት ግንባር የሚል ስያሜ በመስጠት የጋራ ግንባር መሠረቱ። ይህ ግንባር አሁንም በሜ. ጄ. መስከረም አታላይ እየተመራ፤ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ጥቃቶችን አድረሷል። እንደገና ጥቅምት 7 ቀን 1993 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያው ኃይሎች አንድነት ግንባር(በሜ. ጄነራል መስከረም አታላይ የሚመራውን)፣ የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር(በአቶ ተዋት ፖል የሚመራውን)፣ የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(በአቶ ተስፍየ ጌታቸው የሚመራውን) እና የቤኒሻንጉል ነፃነት ንቅናቄ( በአቶ ጁማን ሩፋኤል የሚመራውን) በማቀፍ፣ የአሁኑ የኢትዮጵያ

ሕዝብ አርበኞች ግንባር(ኢ.ሕ. አ.ግ) ተመሠረተ። ዛሬም ይህን ድርጅት በሊቀመንበርነት የሚመራው ሜ.ጄ. መስከረም አታላይ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሥርጎ-ገቦችን፣ አሉባልተኞችን ሳይቋቋም አሁን ካለበት ደረጃ ደረሰ ማለት አይቻልም፤ ሠራዊቱ እንዳመጣጣቸው የተለያዩ ችግሮችን ተጋፍጧል። አሁንም እንደገና ያለሥራቸውና ያለዕውቀታቸው ገብተው አደረጃጀቱንና ታሪካዊ ጉዞውን አገለባብጠው የሚያወሩት ግለሰቦች፣ ወያኔያዊና ዕኩይ ዓላማቸው እንዲሳካ የሚጥሩ ናቸው ብለን እናምናለን።

ውድ ወገኖቻችን ሆይ! ገና በጠዋቱ ይህ ግንባር እንዳይመሠረት ከፍተኛ ሸር ተሠርቷል፤ በወቅቱም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያው ኃይሎች አንድነት ግንባር ጠንካራ የተቃውሞ ድምፁን አሰምቷል፤ በዚህም ምክንያት አመራሮቹ ለእሥር ተዳርገዋል። ከዚያ በኋላም ቢሆን ኢ.ሕ.አ.ግን በርካታ ችግሮች ገጥመውታል፤ በትዕግሥትም መፍትሔ ለመስጠት ሞክሯል። ለምሳሌ ያህልም ኤ.ኤፍ. ዲን መጥቀሱ በቂ ነው እንላለን። አሁንም ቢሆን የሃገራችንን ችግር ለመቅረፍ ፖለቲካዊ መፍትሔዎችን ማቅረብ የግድ ይላል። ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸውና በተግባር ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች ልዩነታቸውን ፈትተው ትብብርን መፍጠር የኢ.ሕ.አ.ግ ዕምነት መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። በትናንሽ ጉዳዮች ላይ ዕድሜልካችንን መፍትሔ አልባ ስንነካከስና ሁካታ ስናሰማ ከመኖር ይልቅ፣ መፍትሔዎችን በማቅረብ ችግርን ፈትቶ ወደ አይቀሬውና ከፍተኛ መስዋዕትነት ወደሚጠይቀው የትግል ዘርፍ መሠማራቱ ይሻላል እንላለን። ግለሰቦች ለምን አስተያየታቸውን ፃፉ ለማለትም አይደለም፤ ሃቅ ግን ተፈልቅቃም ቢሆን ብትወጣ ደስታውን አንችለውም፤ ግለሰቦች ያለኃጥያታቸው እንዲጠቁብን ግን አንፈልግም! ፍትህ ሁሉንም በዕኩልነት ታገልግል እንላለን!

ኢ.ሕ.አ.ግ ብዙኃኑን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ከሕዝብ ጎን ሆኖ ይታገላል እንጂ፣ የሕዝብን ሥልጣን ነጥቆ፣ በኢትዮጵያውያን ላይ መኮፈስ የሚሉት መርሃ-ግብርም ይሁን ራዕይ ከቶ የለውም። ሥልጣንንም ኢትዮጵያዊ ላልሆነ አሻግሮ መስጠት ከንቱ ቅዥት ሆኖ ይቀራል እንጂ፣ ኢትዮጵያውያን በምንም መልኩ እንደማይቀበሉት አሳምረን እናውቃለን። በዚህም ምክንያት ሥነ-ምግባር ተከትሎ ለመሥራት የሚሳናቸውን፣ በሥራቸው የሚያገለግሉትን አባሎች ወይም የሥራ ባልደረቦቻቸውን የማያከብሩ ዘላፊዎችንና ሃሜተኞችን፣ ስልጣንና ንዋይ ወዳዶችን፣ በሙስና የተዘፈቁትን፣ ሕገ-ወጦችን፣ ሥርጎ-ገቦችን፣ አጎብዳጆችን፣ ሰው-በላ ገፀ-ባሕርይ የተላበሱትን፣ ጣዖት አድርጉንና ስገዱልን የሚሉትን ትናንሽ አምባገነኖች፣ በጋራ መክሮ መወሰን የሚሳናቸውን ኢ.ሕ.አ.ግ አምርሮ ይታገላቸዋል፤ ታግሏቸዋልም። እኒህንና ሌሎች ያልተጠቀሱ ድክመቶችን መዋጋት ለምናስበው የኢትዮጵያ ትንሳዔ መሠረቶች ናቸው ብለንም እናምናለን። መጪው ትግል ያማረ እንዲሆንልን፣ ሁሉን ማድረግ የማይሳነው ፈጣሪያችን ይርዳን!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
አንድነት ኃይል ነው!!